# አርባ ዓመት ተጠጋ ፤ ከረሃብ ሣንወጣ!

ትምህርት ቤት ለክረምት ተዘግቷል፤ ለሞያ ማሻሻያ ኮርስ አዲስ አበባ መጥቼ ነው። ዓመተ ምህረቱ ነሐሴ 1967 በመርካቶ ምዕራብ ሁቴል ነበር። የምሳ ሰዓት ስለነበር፣ የጦም ምግብ አዘዝኩኝ፤ ምን ልንገራችሁ የቀረበው ምግብ ሁለት ሰው የሚመልስ ነው። በትሪ በቀረበው የማኛ ጤፍ ላይ የሱፍ ፍትፍት፣ ጎመን፣ ሲሊጆ፣ የሽንብራ ቁሌት፣ የቃሪያ ሥንግ፣ የምስር፡ የአተር፡ አልጫና ቀይ ወጥ እናም ግማሽ ክንድ የሚሆን የዝዋይ አሣ ተጠብሶ ከሎሚ ጋር ቀርቧል። በባለጆሮ ብርጭቆ ድራፍት አዝዣለሁ። ብቻዬን ነበርኩ። በሁለተኛው ፎቅ ላይ ያለው ምግብ ቤት ጢም ብሏል። ጫጫታው ያስተጋባል ፤እኔም ከያይነቱ ቀማመስኩ፤ ከድራፍቱም አንደ ሁለቴ ተጎነጨሁ፤ አገሳሁ፤ ሰውነቴን አዝናናሁ፤ ቀና ብዬ የተከፈተውን ቴሌቪዥን ተመለከትሁ።አዮ ናት (እናት) በኦጋዴን በረሃ ግመሏን እየመራች ሣለች በጠኔ ተጥመልምላ ከግመሉ ፊት ስትወድቅ አየሁኝ። የምግብ ፍላጎቴ ታወከ፤ልቤ በሐዘን ተሞላ፤ እንባዬ በጉጬ ላይ ኩልል ብሎ ወረደ፤ መመገቡን አቆምኩ፤በመሐረብ እንባዬን ጠራረኩ።

አዮና ያ ግመል ለእኔ የቆየ ትዝታ አላቸው። ተወልጄ ባደኩበት የአውራጃ ከተማ ቅዳሜና ማክሰኞ የገበያ ቀናት ሲሆኑ ገበያውን የምታበሽብሸው አዮ ናት። ስለዚህ አዮ ሸንኮራውን፣ ሙዙን፣ ብርቱካኑን፣ ዜይቱናውን፣ ቡናውን፣ ማሩን፣ ቅቤውን በግመሏ ጭና ወደገበያ እንዳልመጣች ሁሉ ፤ዛሬ የእርዳታ ሕል ፍለጋ ወደ ከተማ ሰትመጣ በጠኔ እንደወደቀች ተሰማኝ።

ልጆች ሆነን እናታችን ሙዙን ወይም ሸንኮራውን ሳትገዛልን ሰትምጣና ስናለቃቅስ የሙዝ እናት ሞተች ስትለን እንተከዛለን። የሙዙንና የሸንኮራውን ጥያቄ እንረሳዋለን። ይሄኛው ግን አይረሳም፣ እውነተኛ ሞት ነበረ። አለቀስኩ፣ እንባ አይገደኝ።ግማሽ አካሌ ተቆርሶ የተወሰደ ያህል ተሰማኝ። ወደክፍለ ሃገሬ እንደተመለስኩ ወደ ትምህርት ቤቶች ጽፈት ቤት ሄድኩ፤ከደመወዜ ላይ በየወሩ ሃያ ብር ለድርቅ እንዲቆረጥ ማመልከቻ አቀረብኩ። ብዙም ሳይቆይ ከማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የወር ደመወዝ በዓመት ለድርቅ ገቢ እንዲሆን አዋጅ ወጣ።ቅር ያለው ዜጋ አልነበረም። ለጊዜውም ቢሆን የአእምሮ እረፍት የሚሰጥ ነበር። ሆኖም ግን ዘለቄታዊ መብትሔ እንዳልነበረ ለጥቂቶች ግልጽ ነበር።

ብዙም ሳይቆይ አዲስ ዘመን ጋዜጣ አንድ የአሜሪካ የምርምር ተቋምን ጠቅሶ 'ኢትዮጵያ ለሰላሳ ሦስት ዓመት ትራባለች' የሚል በመጀመሪያ ገጹ ላይ አወጣ። በአንድ ጎኑ ተስፋ አስቆራጭ ቢመስልም በሌላ ጎኑ እንዴት በማለት እልህ የሚያስገባ ነበር። ሁለት የዓለማያ ኮለጅ ተመራቂ ዎች በእርሻ ልማት ላይ በስዊድን ተራዶ ይረዳ በነበረው ኢቢድ በሚበላው ይሰሩ የነበሩ ከአሜሪካ ተቋም የተጠቀሰውን ትንበያ አልተቀበሉትም። የደርግ የመሬት ለአራሹ አዋጅ አልተዋጠላቸውም። ከፈረሱ በፊት ጋሪው በሚል በአጬሩ ያስቀምጡታል። የኢትጵያን ሕዝብ በመሬቱ ጉዳይ ያላሳተፈ አዋጅ የፖለቲካ ፍጆታ ነው ይሉታል።ያም ሆነ ይህ ግብር ከፍሎ ወተት እንደውሃ በቧንባ አቅርቦ በዓለማያ ኮሌጅ ያስተማራቸው ሕዝብ ውለታ አለባቸው። የሚሞት አውሬ ሲፈራገጥ እስኪሞትለት ድረስ በአዛፍ ላይ አርፎ እንደሚጠባበቅ ጆፌ አሞራ ያለሥራ በቀብጺ ተሰፋ መቀመጥ ወንጀል ነው በማለት ለሥራ ተነሣሱ። 'ኢትዮጵያ ሰላሳ ሦስት ዓመት ትራባለች' ማለት ሰላሳ ሦስት ዓመት ተመጽዋች ትሆናለች ማለት እንደሆነ ወሰዱት። ሸሚዛቸውን ጥቅልለው ለሥራ ተሰማሩ፤ የተወረሱ ኩዳድ እርሻዎች ጦም ላለማሳደር፤ ዝናብና ፀሐይ የሚፈራረቅባቸውን ትራክተሮች ለማቀሳቀስ፤ ከግብር ከፋዩ ለሚከፈላቸው ደመወዝ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ሆነው ቀረቡ። የተወረሱ ትራክተሮችን ተጠቅመው ያንን ኩዳድ መሬት ስንዴ ነሰነሱበት። በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ኩንታል ስንዴ አመረቱ። መንግሥትን ቤሳ ቤቲን አላሶጡትም።

አንደኛው ወጣት ሁለት መቶ ሺ ኩንታል ሰንዴ ሲያመርት ሌለኛው በሚኖርበት አውራጃ መቶ ሃምሳ ሺ ኩንታል አመረተ። ሁለቱም ይህ ስንዴ በረሃብ ለተጠቁ አካባቢዎች አንዲላክ ለቤሔራዊ ሐብት ልማት በሰነድ አስረከቡ። የቤሔራዊ ሐበት ልማት በመጓጓዝ ላይ እንዳለ በክረምት ምክንያት ማጓጓዙን ያቋርጣል፤ መቶ ኩንታል የማይሞላ በመጋዘኑ ውስጥ በዝንብ ጠፈጠፍ ተበላሸ። ከአዲስ አባባ የቴሌቭዥን ቀራጮች መጥተው በካሜራ ከቀረጹ በኋላ በኤኮኖሚ አሻጥር ሰም ለሕዝብ ቀረበ። ለወገንና ለሃገር ክብር ለሠሩት መልካም ሥራ፤ ነጋሽ ሰሐሌ በባሌ ጎባ ፣ ታደሰ ይርገጤ በአዲስ አበባ በእርሻ ሚኒስተር ጽፈት ቤት አካባቢ ካሳችስ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ።
ነጋሽና ታደስ በአሜሪካ አገር የነፃ ትምህርት ዕድል በጊዜው ቢሰጣቸውም፣ያለን ዕውቀት ከሃገራችን ገበሬ ጋር ለመሥራት ቢቂያችን ነው ነበር መልሳቸው፤ ቤተሰብም ያንን ያህል ደመወዝ እያገኙ ትዳር መስርተው ልጅ ወልድው ቢያሳኞቸው ቢማጸኗቸውም አለሆነም። ሃገር ሰላሳ ዓመት ትራባለች እየተባለ ልጅ ወደዚህ ዓለም ማምጣት ለረሃብ ነው? ነበር መልሳቸው። አርባ ዓመት ተጠጋ ከረሃብ ሳንወጣ፤ በቅርቡ ለሕውሃቱ መሪ ለአቶ መለስ ዜናዊ የሃገራችንን የረሃብ ተመስሌነት አስመልክቶ ከጋዜጠኛዋ ለቀረበላቸው ጥያቄ የመለሱት መልስ አሣዝኖኝ ነው ይህቺን ጽሑፍ ለማቅረብ የተነሣሣሁት። ጥያቄው ይህን ይመስል ነበር፤ በኢንግሊዘኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ውስጥ 'ረሃብ' (Hunger) ለሚለው '

‘ኢትዮጵያ’ ፊቺ ቃል ሆናለች። ምን ይላሉ?” የሚል ነበር። መልሱም ‘ የላሊበላን ገዳምን የቀረጸ፣ የፋሲልን ግንብ የገነባ፣ የአክሱምን ሐውልት ያቆመ ሕዝብ እንዴት እራሱን መመገብ ይሳናዋል?’ በሚል ጥያቄን በጥያቄ ነበር የመለሱት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን ራሱን መመገብ እንደተሳነው፤ ለአቶ መለስ ዜናዊ የጠፋቸው ባይሆንም አንዳንድ ነገሮችን ላስታውሳቸው። በጋንቤላ ፣ በኦጋዴን፣ በአዲስ አበባ የአጋዚ ጦራቸው በዓለም ሕዝብ ፊት ጭፍጨፋ ያከሄደባቸው ሥፍራዎች ናቸው። በነዚህ ሥፍራዎች የሚኖረው ሕዝቡ በቀን አንዴ ከተመገበ እሰየው ነው። ደግሞ የሕውሃቱ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ የዘነጉት አንድ ነገር አለ፤ በአምስት ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ መለስ ዜናዎች በየ ቀበሌው፣ በየወረዳው፣ በየአውራጃው፣ በየክፍለሃገሩ እንዳሉ ነው። እርሳቸው በቴሌቭዥን መስኮት ወጥተው ጣት እቆርጣለሁ ሲሉ፣ አምስት ሚሊዮኑ ተቀጣሪያቸው ካራ ሲስል ያድራል። ጣት ለመቁረጥ አይደለም። አንገት ለመቁረጥ። ይፍረዱን በፍረሃት የተወጠረ ሕዝብ እንዴት እራሱን ይመግባል?

ሁለቱን ወጣት ገበሬዎች የጠቀስኩት ፍትሕ በሃገራችን ቢሰፍን ታምር እንደምንሰራ ለማሳየት ነው። ፍትሕ ያለመኖሩ ያስከተለው ጉዳት ረሃብ ብቻ አይደለም፤ እንደሰው ማሰብ እንዳንችልም ጭምር ነው። ዩኒቨርሲተዎች ቢከፈቱ ፤ አውራ መንገዶች ቢዘረጉ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ቢሰሩ ፍትህ ከሌለ እንደ እሰሳ መታጎሪያ በረት ወይም ጋጣ ናቸው። የሚያስገርመው አቶ መለስ ዜናዊና ጓዶቻቸው ከአርባ ዓመት በፊት ደደቢት በረሃ የገቡት ምን ፈልገው እንደነበር እስካሁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ አይደለም። አቶ መለሰም ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ግልጽ ያደረጉት ነገር ቢኖር ሕዝብን በጎሣ መከፋፈል ቀድሞንም በአእምሮቻው የቋጠሩት የአማራ ሕዝብን ጥላቻ ተግባራዊ ሲያደርጉ ነው። ለአቶ መለስ ዜናዊ በ1997ዓ ም ሰኔ ወር ላይ የሆነውን ላሰታውሳቸው፤ መሪም አባትም ናቸው።አንደ አባት በሻራተን ሆቴል የልጃቸውን ምረቃ ሲያከብሩ በክንዳቸው ልጃቸውን እንዳቀፉ ካሜራው ያሳያል። እሰየው ነው። የሰውን ባህሪ ያሳያል። ከሆቴሉ ውጭ ግን በእርሳቸው ትዕዛዝ የአጋዚ ሠራዊት ሰላማዊ ሰልፍ የወጣውን የአዲስ አበባን ሕዝብ ይገላል። በአጋጣሚ የተገኘ የአስራ አንድ ዓመት ወጣት ባንክ ሲዘርፍ ተገኘ ተብሎ በአጋዚ ጦር ተገደለ። አቶ መለስ የተገደለውን የአስራ አንድ ዓመቱን ነብዮን እናት ለምን ሻራተን አዲስ ልደቱ አላከበሩለትም ሊሏቸው ይገባል? የኢትዮጵያን ሕዝብም እንዴት እራሱን መመገብ ተሳነው ሲሉ ያ ማለቶ ነው። የኦጋዴን ሕዝብ ዳቦ እያለ ሲጮህ ለምን ኬክ አይበላም ማለት ይመስላል።

ምንም እንኳን የውሕሃቱ መሪ አቶ መለሰ ዜናዊ በኢንግሊዘኛው ቋንቋ (**victimizing the victim**) ተጎጂውን ጎጂ አድርገው ቢያቀርቡትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትሕ አጥቷል። ፍትሕ የሌለው ሕዝብ ዜጋ አይደለም። ዜጋ የሚበለው የራሱ የሆነ ሃገር ሲኖረው ብቻ ነው። ሃገሬ የሚለው መብቱ ተጠብቆለት የዜግነቱን ግዴታ ሲወጣ ነው። በአፄ ኃይለ ሥላሴ በደርግ መንግሥት ብንራብ ፍትሕ ቢጓደልብን በሁላችን ላይ የተጫነ ቀንበር ስለነበር በሕብረት ታግለነዋል። በጋራ ቀንበሩን ከጫቃችን ላይ አሽቀጥረን ለመጣል በሒደት ላይ ነበርን።
የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ግን ሁኔታዎች ተለዋወጡ። የዘር ፖለቲካ ነገሠ፣ አገራዊ ራዕይ ኮሰሰ ፤ ርዕስታችን ለባዕዳን ተሸጠ፣ ዜጎች ሃገራቸውን ለባዕዳን ለቀው ተሰደዱ፤ በችግር ጊዜ ሊቆሙለት ሊያጽናኑት የሚገባቸው የሃይማኖት መሪዎችም ሥጋቸው አሸነፋቸው ፤ ለጥሩ ኑሮ ተሰደዱ፣ በጎቻቸውን ለተኩላ ትተው። ቀደሞውንም በሃገራችን የተዘረጋው የትምህርት ሥረዐት የራስን ምቾት ከማደላደል ያለፈ፣ አርቆ አስተዋይነትን መሠረት ያደረገ አልነበረም። ስለዚህ ተማርኩ የሚለውም ክፍል ቢሆን በቀላሉ ለቅጦት ኑሮ፣ ለአላቂ ዕቃ፣ ተበረከከ፤ ለጥቅም ስዕብናውን አሳልፎ ሰጠ። በሃገር ቤት የቀረው ሕዝብም ቢሆን በረሃብ እንደቅጠል እየረገፈ ነው። በአዲስ አበባ የሚገኙት የመገናኛ ብዙሃን ስለ ውሸት እድገት እንጂ በኦጋዴን ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ረሃብ ለሌሎቹ የሃገሪቱ ክፍሎች አያሰሙም። በተለይ በኦጋዴን የመገናኛ ብዙሃን አይሉም።የእርዳታ እህል እንዳይደርስ ታግዷል። የሠራዊቱም ተልኮ ይህን ማስፈጸም ነው። የሃገራችን አሁን ያለችበት ሁኔታ ሱማሊያ በኤሮፓ አቆጣጠር በሰማኒያው ዓመተ ምህረት ውስጥ የነበረችበት ሁኔታ ያስታውሰናል። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር እያከናወነ ያለው በሰማኒያው ዓመተ ምህረቶች ውስጥ የሱማሌው ፕሬዘዳንት ዚያድ ባሬ ያደርግ የነበረውን ነው። ዚያድ ባሬ ለም መሬቶችን ለአረብ ሐብታሞች አከራየ፤ ያልተመረመሩ ማደበሪያዎችን ተጠቅመው ለጊዜው መሬቱን ምርታማ አደረጉት። ግን የክራይ መሬት ነውና ለዘለቄተው ለሚያስከትለው ጉዳት ደንታ አልሰጣቸውም። ዛሬ ለሱማሌ ሕዝብ የቀረው አመዱ ነው። ጭንጫ መሬት ምንም የማያበቅል ። በተጨማሪ በስልጣን ለመቆየት ሕዝቡን በጎሣ ከፋፈሎ ከዘርያዎቹም ታማኞቹን ከግመል ጠባቂነት ከመንገድ ጠራጊነት አንስቶ የጅንራልና የባንክ ገዥነት ሥልጣን ሰጣቻው። የሃገሪቱን ሐብት በቆጥጥሩ ሥር አዋለ። ከግመል አንስቶ እስከ ፍየልና በግ ንግድ የራሱን ጎሣዎች አሰማራ። ገንዘቡ እየተሰበሰበ በአረብ ባንኮች ተከማቸ። ‘ ፈረሰኛ ሲቀድም እግረኛ ምን ይጠብቃል ?’ ሆነና ሕዝቡ የራሱን ሃገር ሐብት ዘረፋ ላይ ተሰማራ። የዛሬዋ ሱማሊየ የዚያን ጊዜው ውጤት ናት። የሚዘረፈው ሲጣፋ መሪውም ሲኮበልል ቀሪው እርስ በእርስ መገዳደልና ረሃብ ነው።ዚያድ ባሬም ቢሆን የዘረፈውን ገንዘብ አልበላውም። ሃገሩንም ሕዝቡንም ይዞ መቀብር ወረደ። ማንም ኢትዮጵያዊ ሃገሩ እንደሱማሌያ እንደትሆን አይመኝም። ምኞት ደግሞ እንዳትሆን አያግዳትም። እንዳይሆን የምናስቆመው እኛ ልጆቿ ነን።

ሐቁ ግን የሕውሃት መንግሥት ኢትዮጵያ እንደሱማሌያ እንደትሆን በማመቻቸት ላይ ነው። ይህንንም የጀመረው ከ ዘጠና ሰባቱ ምርጫ በኋላ ነው። ለምን ፈለገ? ሕዝብ በጎሣ ተከፍፍሎ ሲዋጋ አቶ መለስና የቅርብ ቤተሰባቸው ኢትዮጵያን ለቀው ይወጣሉ ወይም ሱማሌ ላንድ ከትልቋ ሱማሌያ ተገጥላ መንግሥት እንደመሠረተችው ሁሉ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሣ ተከፋፍሎ ሲገዳደል ትግራይን አስገጥለው ዞር ሊሉ እንደሆነ ምልክቶች እየታዩ ነው። የተዘረፈው ከ 8 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወደ ውጭ ያሸሹት፤ ከባንክ የተዘረፈው አስር ኪሎ ወርቅ ፤ ከመጋዘን የተዘረፈው አስር ሺ ቶን ቡና፤ ለሕዝብ ያልተገለጸው የመሬት ሽያጭ ፤ኤፈርት የሚሉት ድርጅት ካፒታል በአባይ ግንባት ስም የሚሰበሰበው ገንዘብ ለተረበው የኢትዮጵያ ሕዝብ ካልዋለና ታንክ ከተገዛበት ይህ ሁሉ አንድ ቦታ ላይ ማረፍ አለበት። የት? ብለን መጠየቅ አለብን። በሌላ መልኩ ለፈጸሙት ግድያ በወንጀለኛነት የሚጠይቃቸው ክፍል እንደይኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸታቸው እንደሆነ ምልክቶች ይታያሉ። ዚያድ ባሬ ያደረገው ይህንኑ ነው።

የሰቆቃው ገፈት ቀማሹ አሁንም ወደ ፊትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ነገሮች ይበልጥ ውስብስብ ሆነው ውሉ ከመጥፋቱ በፊት ሃገራችንን በባለቤትነት ወደ እጃችን መመለስ አለብን። ሁኔታው ጊዜ የሚሰጥ አይደለም። ያልገበው እስኪገባው ስንጠብቅ የሃገራችን ሁኔታ ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን ነው። በግንቦት ሰባት፣ በኦነግና በኦንለፍ ከአፋርና ከፍትሕ ፈላጊዎች ጋር የሚደረገው ውይይት ሰፍቶ በሃገራችን በሕዝቡ ውስጥ እንዲጀምር ማድረግ ጊዜው አሁን ነው። የገባን ወገኖች ያልገባቸው እስኪገባቸው አንጠብቅ ። የገባን እጅ ለእጅ ተያይዘን ሃገራችንን እናድን። ሃገር ሲኖር ነው አመራር የሚኖረው። ውርደት 'በቃ' ብለን እንነሳ!

እግዚአሕብሔ ኢትዮጵያን ይጠብቅ።

ታደለ መከሪያ